# መቼ ነው የምንነሳው?

ሸዋዬ ኪሮስ[1]

የተከበራችሁ ውድ ወገኖቼ

የዛሬ አምስት ዓመት በአሰቃቂ ሁኔታ እና በጭካኔ ህይወታቸውን ላጡ፤ አካላቸው ለጎደለ እና ሰቆቃዎች ለደረሰባቸው ወገኖቻችን መታሰቢያ በተዘጋጀ ዝክር ላይ ተገኝቼ አጭር ንግግር እንዳደርግ ስለጋበዛችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ።

በ1997 ዓም ወደ ምርጫ ስንገባ በሰላማዊ መንገድ በምርጫ ካርዶቻችን ገዢዎችን ሽረን መሪዎቻችንን እንመርጣለን የሚል ተስፋ ነበረን። ይህ ተስፋ ነበር ብዙዎቻችንን ወደ ፓለቲካ የሳበን። የ1998 ምርጫ ለኔ ለመመረጥ ብቻ ሳይሆን ለመምረጥም የመጀመሪያዬ ነው። ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ የነበረኝ ፍላጎት የጀመረው ከልጅነቴ ጀምሮ ነው። በተለይም ለጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ከፍተኛ አድናቆት ስነበረኝ በፍርድ ቤቱ ከተናገሩት ውስጥ አብዛኛውን የሁለተኛ ደረጃ  ተማሪ እያለሁ አውቀው ነበር። እንዲህ ብለው ነበር ...

> *“እናንተ ዳኞች! የበየናችሁብኝን የሞት ፍርድ ያለ ይግባኝ ተቀብያለሁ። ይግባኝ ብዬ የሚመለከትልኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢሆን ኖሮ ይግባኝ ማለት በፈልኩ ነበር። ነገር ግን ይህ እንደማይሆን አውቃለሁና የዓፄ ኃይለ ሥላሴን ፊት ለማየት አልፈቅድም። በእግዚአብሔር ስም በተቀመጣችሁበት የፍርድ ወንበር ላይ ከመቀመጣችሁ በፊት በእኔ ላይ የምትሰጡትን ፍርድ ታውቁት እንደነበር ሳስበውና ፍርድ እስከዚህ መድረሱን ስታዘብ ኀዘኔ ይብሳል። ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት፣ ነጻነትና እርምጃ የተነሳሁ ወንጀለኛ ነኝ እንጂ ላፋጀው የተነሳሁ ወንበዴ አይደለሁም። ይህን ማድረግ ፈልጌ ቢሆን ኖሮ ማንም የማይወዳደረው ሠራዊትና መሣሪያ ሳላጣ ዛሬ ከእናንተ ፊት ለመቆም ባልበቃሁ ነበር። እኔ ከዓፄ ኃይለ ሥላሴ ድንክ ውሾች ያነሰ ደመወዝ የሚያገኙ ሁለት የተራ ወታደሮችን አጣልቼ ለማደባደብና ሀገር ለማፍረስ አለመነሳሳቴን የሚያረጋግጥልኝ ከእናንተ በትዕዛዝ ያገኘሁትን ፍርድ ለመቀበል እዚህ መቆሜ ነው። የጀመርኩት ሥራ ቀላል አይደለም። ነገር ግን አልተሸነፍኩም። ወገኔ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የጀመርኩትን ሥራ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ፈጽሞ እራሱን እንደሚጠቅምበት አልጠራጠርም። ባጭሩ በእኔ ላይ ለመፍረድ የቻኮላችሁትን ያህል አሥር እና አሥራ አምስት ዓመት የምታጉላሉት የድህውን ሕዝብ ጉዳይ እንደዚህ አፋጥናችሁ ብትሠሩትና ብትሸኙት ኖሮ የእኔ መነሳት ባላስፈለገ ነበር። ከእናንተ ከዳኞችና የሞት ፍርድ እንድትበይኑብኝ ካዘዛችሁ ሰው ይልቅ ፍርድ ተቀባይ የዛሬው ወንጀለኛ የነገው ባለታሪክ ነኝ።”*

ይታያችሁ ይህ የተባለው መጋቢት 19 ቀን 1953 ዓም ነው። የዛሬ ሃምሳ ዓመት!!! ያኔ መንግሥቱ ንዋይ የጀመሩት ሥራ ቀላል አለመሆኑ፤ ቀጣዩ  ትውልድ ደግሞ ያንን ዓላማ  እንደሚያሳካ እርግጠኛ  ነበሩ። ዛሬ ከሃምሳ አመታት በሁዋላ ከያኔው እጅግ በባሰ በፍትህ እየተቀለደ መሆኑን ማን በነገራቸው?

---

[1] ኖቬምበር 8 ቀን 2010 ለንደን በሰማዕታት መታሰቢያ ስብሰባ የቀረበ

እሳቸው እንዲህ ዓይነቱን ሃይለቃል ፍርድ ቤት ውስጥ ተናገሩ። ከ45 ዓመታት በኋላ በ1998 እንደሳቸው ሁሉ የተሟላ ኑሮዓቸዉን ትተዉ ለአገር አንድነትና ነፃነት የታገሉትን የቅንጅት መሪዎቸ በተከሰሱ ጊዜ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ተከሳሾችን በመወከል ንግግር ለማድረግ ሲጀምሩ "አቁም ፍርድ ቤት የቅስቀሳ መድረክ አይደለም" ነበር የተባሉት፡፡ ይህ ብቻውን ከፍትህ አኳያ ምን ያህል ወደ ኋላ እንደሄድን ያመለክታል፡፡

መንግሥቱ ንዋይ ለአገር አንድነትና ለነፃነት መታገላቸውን ገልፀዋል፡፡ ዛሬ በሁለቱም ከያኔው በባሰ ሁኔታ ላይ እንገኛለን፡፡ ዘረኝነት የመንግሥት ፖሊሲ ሆኖ እያመሰን ነው፡፡ ዛሬ አገራችን አንድ አገር መሆኗ ራሱ አጠራጣሪ ሆኗል፡፡

ሌላው ጀግናዬ ማንዴላ ናቸው፡፡ ማንዲላን ሳድነቃቸው ኖሬዓለሁ፡፡ እሳቸውን የመሰለ መሪ ያላወጣን መሆኑ የሚቆጭ ቢሆንም ወደፊት ይኖረናል የሚል ተስፋ ግን አሁንም አለኝ፡፡ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል ታሪክም ይማርከኝ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል አገራችን ከምንጊዜውም በላይ ምሁራኖቿን ያጣችበት መሆኑ አሳዛኝ ነው፡፡ ባጭሩ መጠነኛ ዝንባሌ ቢኖረኝም እኔ በፓለቲካ ውስጥ በቀጥታ ተሳትፌ አላውቅም ነበር፡፡

1997 እንዲህ ዓይነቶቹን የተዳፈኑ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ጥማቶች አደባባይ እንዲወጡ አደረገ፡፡ በዚህም ምክንያት ለመጀመሪያ ጊዜ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ፓለቲካ ውሰጥ በተስፋ የሚሳተፉበት መስከ ለመሆን ተቃርቦ ነበር፡፡

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሥልጣንን በጉልበት ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ዘረኝነት በሁሉም ረገድ ተስፋፍቷል። ይሁን እንጂ ለአጭር ጊዜ ቢሆንም ኢትዮጵያ በ1997 የደረሰችበት የመግባባት ደረጃ ላይ ደርሳ የምታውቅ አይመስለኝም፡፡ ሚያዚያ 30 1997 የዚህ ማረጋገጫ ነው፡፡ ግንቦት 7 1997 በየሰው ፊት ላይ ይነበብ የነበረው ተስፋ ለመግለፅ ያስቸግራል፡፡ ወጣቶች በሙሉ ኃይላቸው ፓለቲካ ውስጥ ገቡ፡፡ ሁሉም ሰው "ፍርሃት ደህና ሰንብች" ያለ መሰለ፡፡

ምን ያደርጋል ... ያ ሁሉ መግባባት፤ ያ ሁሉ ተስፋ በወራት ጊዜ ውስጥ እንደ ጉም በኖ ጠፋ፡፡

ሰኔ 97 እና ጥቅምት 98 አዲስ አበባችን እጅግ በሚያስፈሩ እና በተቆጡ ወታደሮች ተወረረች፡፡ ወታደሮቹ ኢትዮጵያዊያን ናቸው ብሎ ማመን ያስቸግራል፡፡ የቻሉትን ያህል ተኮሱ፣ ገደሉ፣ ደበደቡ፣ አሰሩ፡፡ በተስፋ ትፈነቀነቅ የነበረችው ከተማችንን ሃዘን ወርራት፡፡ አዲስ አበባ የጦርነት አውድማ ሆነች፡፡ የአየር መቃወሚያ ባዙቃዎችን የተሸከሙ ወታደሮች መዋዕለ ህፃናት ውስጥ ገብተው ህፃናትን አሸበሩ፡፡ ከተማችን የዋይታና የልቅሶ መዲና ሆነች፡፡ አዲስ አበባ የሆነው ወደ ሌሎች ከተሞችም ተዛመተ፡፡ እስር ቤቶች ተጣበው የጦር ማሰልጠኛዎች እስር ቤቶች ሆኑ፡፡ አዋሽ አርባ፣ ዴዴሳ፣ ጦላይ፣ ወዘተ የዜጎቻችን ማጎሪዎች ሆኑ፡፡ በዚህ ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተመራጭ አቶ ተሾመ ባለቤት ባላቸው ለመታደግ በመሞከራቸው በልጆቻቸውና በጎረቤት ፊት ተገደሉ። ልጃቸው የእናትዋን አስከሬን ለመውሰድ “ቅንጅት ነው የገደላት ብለሽ ፈርሚ” ተባለች። ሌላ አባላችን ደግሞ ሚስቱ ወለደችና ለልጁ "እሪ የፍትህ ያለህ" የሚል ስም አወጣለት፡፡

ከዚያ ጊዜ ወዲህ በሁሉም ረገድ የቁልቁለት ጉዞ ተያይዘነዋል፡፡ ችጋር፣ ረሃብ፣ መከራ፣ ስደት፣ እስርና እንገግልት የዘወትር እጣ ፈንታችን ሆኗል፡፡

የመለስ አገዛዝም ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ እኛንም መሪዎቻችንንም ማዋረድ ሥራዬ ብሎ ተያይዞታል፡፡

በዛሬው እለት ሰማዕታቱን ስናስታውስ ይኸ ሁሉ በጭንቅላታችን መምጣቱ አይቀርም፡፡ ከመንግሥቱ ንዋይ ብንጀምር እነሆ ለሃምሳ ዓመታት ለህግ የበላይነት፣ ለዲሞክራሲ፣ ለነፃነትና እኩልነት የዜጎቻችንን ህይወት ስንገብር ቆይተናል፡፡ መቸ ነው የእነዚህ ሰማዕታት ህይወት ፍሬ የሚፈራው? መች ነው በትንሽ በትልቁ መናቆር ትተን ለጋራ ድል የምንነሳው? መቸ ነው? መቸ ነው? መቸ ነው?

**ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ**